

# የክርስቶስ ትንሳኤ ኃይል



ትምህርት 8 ለነሐሴ 16፣ 2018


“ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት፤. . . . ክርስቶስም
ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ።” (1 ቆሮንቶስ 15:14-17)



እንደ ግሪክ ፍልስፍና አስተሳሰብ በተለይ ደግሞ እንደ ፕላቶ አስተምህሮ የሰው ሥጋ ክፉና ኢሟዋቲ የሆነውን ነፍስ የሚያስር ወይኒ ቤት ተደርጎ ይታሰባል። ከዚህ አስተሳሰብ አኳያ የአካላዊ ትንሳኤ ለግሪኮችና ለሮማኖች የሚሰጠው ትርጉም ምን ነበር?



በዚህ ሳቢያ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ በትንሳኤ የማያምን ቡድን ነበር። ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልዕክቱ ውስጥ በአስራ አምስተኛው ምዕራፍ ይህንን ጉዳይ ይዳስሰዋል።

ይህ ተራ ጉዳይ አይደለም። ትንሳኤ ከመዳን ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው። ትንሳኤ ከሌለ… ወንጌልን መስበክ ጥቅሙ ምን ላይ ነው?

## የኢየሱስ ትንሳኤ

ትንሳኤው ታሪካዊ ክስተት ነበር ወይ?
(1 ቆሮንቶስ 15:1-11)

## የኢየሱስ ትንሳኤ ውጤቶች

ክርስቶስ ከሞት ባይነሳ ኖሮስ?
(1 ቆሮንቶስ 15:12-19)


በትንሳኤው የተረጋገጡ ነገሮች ምንድን ናቸው?
(1 ቆሮንቶስ 15:20-34)

## የእኛ ትንሳኤ

ትንሳኤያችን በምን አይነት ሥጋ ይሆናል?
(1 ቆሮንቶስ 15:35-49)

የእኛ ትንሳኤ የሚሆነው መቼ ነው?
(1 ቆሮንቶስ 15:50-58)

# የኢየሱስ ትንሳኤ



# ትንሳኤው ታሪካዊ ክስተት ነበር ወይ?

"እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ፦ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፥ ተቀበረም፥ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፥" (1 ቆሮንቶስ 15:3-4)

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ስለ ትንሳኤ ያላቸውን ጥርጣሬ ከመዳሰሱ በፊት የወንጌልን አሰራር አስታውሷቸው ነበር (1ቆሮ 15:1-2):

ይሰበካል → ይቀበሉታል → ይጸኑበታል → ድነት ይገኛል

እና የሚሰበከው ወንጌል ምንድን ነው? (1ቆሮ 15:3-4)

ክርስቶስ ለኃጥያታችን ሞቷል → ክርስቶስ ተቀብሮ ነበር → በሶስተኛውም ቀን ተነስቷል

ትንሳኤው በታሪክ ውስጥ ያለ ክስተት መሆኑን የምናውቀው እንዴት ነው? ኢየሱስ ከተነሳ በኋላ ያዩት እነ ማን ናቸው? (1ቆሮ 15:5-8)

ጴጥሮስና አስራ ሁለቱ → ከ500 በላይ ምስክሮች → ያዕቆብና ሐዋርያት → ጳውሎስ


ወንጌል "መጽሐፍ እንደሚል" የተከናወነ የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ጳውሎስ ግልጽ አድርጎ ይናገራል። ይህም ማለት አስቀድሞ የተወሰነ እቅድ ነው፣ ትንሳኤውም በዚህ ውስጥ ዋና ሚና አለው። የሚጠራጠር ሰው ይኖርን? እንግዲያውስ በሰዓቱ በህይወት የነበሩትን የአይን እማኞች መጠየቅ ይችላሉ!








# የኢየሱስ ትንሳኤ ውጤቶች







# ክርስቶስ ከሞት ባይነሳ ኖሮስ?

"ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት" (1 ቆሮንቶስ 15:14)



የትንሳኤውን እውነታ መካድ በክርስትና እምነት ውስጥ ጉድለትን ይፈጥራል፣ ምክንያቱም "ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣማ" (1 ቆሮንቶስ 15:12-13)። እና ኢየሱስ ከሙታን ካልተነሳ...

- የወንጌሉ ስብከት ትርጉም አይኖረውም (1ቆሮ 15:14)
- እምነታችን ከንቱ ይሆናል (1ቆሮ 15:14) ጥቅም አይኖረውም (1ቆሮ 15:17)
- ሐሰተኛ ምስክሮች እንሆናለን (1ቆሮ 15:15)
- አሁንም በኃጥያታችን አለን ማለት ነው (1ቆሮ 15:17)
- የሞቱትም መቼም ወደ ሕይወት አይመለሱም (1 ቆሮ 15:18)



ትንሳኤው ከለሌ ኢየሱስ ያለ ምክንያት የተገደለ አንድ ተራ ፃድቅ ሰው እንጂ አዳኝ አይሆንም። "አሁን ግን ክርስቶስ . . .ከሙታን ተነሥቶአል።" (1 ቆሮ 15:20)። ሕያው የሆነ አዳኝ አለን።

በዚህም ምክንያት ወንጌሉ እንዲሁም እምነታችን ትርጉም አለው፤ እኛም እውነተኛ ምስክሮች ነን፤ ኃጥያታችን ይቅር ተብሎአል፤ እናም በክርስቶስ ሆነው የሞቱት ዳግም በሕይወት ይኖራሉ።



# በትንሳኤው የተረጋገጡ ነገሮች ምንድን ናቸው?

**"አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል።" (1 ቆሮንቶስ 15:20)**



በኢየሱስ ትንሳኤ የተረጋገጠው የመጀመሪያው እውነታ ከአዳም እስከ መጨረሻው ሰው ድረስ የመዳንን እውነት የተቀበልን ሁሉ ብንሞት ዳግም ትንሳኤ እንደሚኖረን ነው (1ቆሮ 15:20-23)።



ከትንሳኤያችን በኋላ ምን ይሆናል? ኢየሱስ ሞትን አሸንፎ ጠላቶቹን ሁሉ ይረታል (1ቆሮ 15:25-26)። ከዚያም ኢየሱስ ሁሉን ነገር ለአባቱ ያስገዛል "እግዚአብሔርም ሁሉ በሁሉ" ይሆናል (1ቆሮ 15:24፣ 28)።

ከተረጋገጡት ከእነዚህ የወደፊት ክስተቶች በተጨማሪ ጳውሎስ የየዕለት ሕይወታችንን የሚነኩ ሁለት ነገሮችን አረጋግጦልናል:



1 ቆሮ 15:30-32

መከራና አደጋ ቢኖረውም ወንጌልን መስበክ ያዋጣል።



1 ቆሮ 15:33-34

ከመጽሐፍ ቅዱስ መርሆዎች ጋር ራስን አስማምቶ መኖር ያዋጣል።

# የእኛ ትንሳኤ



# ትንሳኤያችን በምን አይነት አካል ይሆናል?

“የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፥ ባለመበስበስ ይነሣል” (1 ቆሮንቶስ 15:42)

በትንሳኤ ስለሚኖረን አካል የተነገሩ ምሳሌዎች:

## የእፅዋት አካል (1ቆሮ 15:35-38)

ዘር ይዘራል



ሰብሉ ይታጨዳል



እግዚአብሔር ለሁሉም ተክል የፈለገውን አካል ይሰጠዋል



## ተንቀሳቃሽ አካላት (1ቆሮ 15:39)

የሰው አካል



የእንስሳት አካል



የአሳ አካል



የወፍ አካል



## የሰማይ አካላት (1ቆሮ 15:40-41)

የጸሐይ ክብር



የጨረቃ ክብር



የከዋክብት ክብር



እያንዳንዱ የራሱ ክብር አለው




# ትንሳኤያችን በምን አይነት አካል ይሆናል?

“የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፥ ባለመበስበስ ይነሣል” (1 ቆሮንቶስ 15:42)

አሁን በለበስነው ሥጋና በትንሳኤው አካላችን መካከል ምን ልዩነት አለ?
(1ቆሮ 15:42-44)

| የአሁኑ አካላችን | የትንሳኤው አካላችን |
|---|---|
| በስባሽ | ፍጹም |
| የረከሰ | የከበረ |
| ደካማ | ኃይለኛ |
| ሥጋዊ | መንፈሳዊ |







አዳም ምድራዊ አካል የነበረው ሲሆን ሁለተኛው አዳም ኢየሱስ ሰማያዊ አካል አለው። በትንሳኤው ጊዜ አካላችን ፍጹም የሆነውን፣ የከበረውን፣ ኃይለኛውን፣ መንፈሳዊውንና ሰማያዊውን የክርስቶስ አካል ይላበሳል (1ቆሮ 15:45-49)።

# የእኛ ትንሳኤ የሚሆነው መቼ ነው?

“እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን” (1 ቆሮንቶስ 15:51)



ጳውሎስ የሙታን ትንሳኤ መች እንደሚሆንና አካላችን እንዴት እንደሚለወጥ ከመናገሩ በፊት “ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ” እንደማይችሉ አስቀምጦ ነበር (1ቆሮ 15:50)። ታዲያ ይህ ማለት ከትንሳኤ በኋላ የሚጨበጥ አካል አይኖረንም ማለት ነው?

“ሥጋና ደም” የሚለው ቃል ሰውነትን ለመግለጽ እንደ ተለዋጭ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላል (ማቴ 16:17፣ ገላ 1:16፣ ኤፌ 6:12፣ ዕብ 2:14)። ጳውሎስ ነገሮችን እያስተያየ የምድር ነዋሪዎችን እንደ ብልሹ፣ የሰማይን ነዋሪዎች ደግሞ እንደ ፍጹም አድርጎ ያቀርባል። በምድር ያለን አካል የሚበሰብስ ስለሆነ ሰማይ ይዘነው ልንገባ አንችልም።



ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ በስባሹ አካል ወደማይበሰብስ አካል ይለወጣል፣ ይህ አካል ኢየሱስ በትንሳኤው የተላበሰው አካል ነው (1ቆሮ 15:51-55፣ ሉቃ 24:36-40)።

በኢየሱስ የሚያንቀላፉት ሰዎች እስከ ምጽዓቱ ቀን ድረስ ብዙ ጊዜ ማለፉ አይታወቃቸውም፤ ነገር ግን ከሞቱበት ቅጽበት ብዙም ሳይቆይ ኢየሱስን ሲመጣ ያዩታል (1ቆሮ 15:52)።





EGW (The Faith I Live By, June 23)

“የኢየሱስ ትንሳኤ በእርሱ አንቀላፍተው የመጨረሻውን ትንሳኤ ተካፋይ ለሚሆኑት እንደ ምሳሌ የሚሆን ነው። አዳኙ የተነሳበት አካል መልኩና የአነጋገሩ አኳሃን ተከታዮቹ የሚያውቁት የቀድሞው ነበር። በኢየሱስ የሚያንቀላፉት ሁሉ እንደዚሁ ይሆናሉ። ደቀመዛሙርት ኢየሱስን እንዳወቁት እኛም ወዳጆቻችንን ያን ጊዜ እናውቃቸዋለን። አካላቸው በምድር ኑሮ ተጎድቶ የነበረ፣ የታመመ ወይም የተጎሳቆለ ቢሆንም በትንሳኤ በከበረው አካል የየግል መልካቸው የተጠበቀ ይሆናል፣ እና ከኢየሱስ ብሩህ ፊት በሚያንጸባርቀው ብርሃን የወዳጆቻችንን መልክ ለይተን እናውቀዋለን።”